# ጥላቻን ወደ አዲስ ሳይንስ ሰቅሎ፡ የመቻቻል ጠፋ ከንቱ ጩኸት

በኢትዮጵያ ዙሪያ የሚነሱና የሚወድቁ የፖለቲካ ቅኝቶችን ለመዳሰስ ይረዳኛል በሚል ከተነሱላት ጀምሮ እስከ ተነሱባት የተደረደሩ የኢትዮጵያ ድህረ ገፆችን ማገላበጥ እወዳለሁ። በዚሁ አጋጣሚ ሰሞኑን ሞረሺ የመረጃ ማዕከል የሚለውን ገፅ ጎራ ብየ ስመለከት አይኔን የሳበ "**ተደብቆ የቆየው ሌላው የኢህአፓ ታሪክ ገጽታ – በዶክተር አሰፋ ነጋሽ**" (ከዚህ ቀጥሎ ዶ/ር ብየ በምጠራቸው) በሚል ርዕስ የቀረበና የሁለት የቀድሞ ኢሕአፓ ዓመራር ዓባላት የነበሩት የብርሃነ መስቀል ረዳንና ጌታቸው ማሩን ፎቶግራፍ የለጠፈ ፅሁፍ አነበብኩ። ፅሁፉን በጥሞና ስመለከተው ፀሃፊው በርዕሳቸው ዙሪያ ማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት ሳይሆን ለያ ትውልድ ራዕይ ያላቸው ጥላቻ እንዴት መንፈሳቸውን እንዳናወጠውና እረፍት እንዳሳጣቸው ከቋንቋ አጠቃቀማቸው ጀምሮ መረዳት ይቻላል። ከፖለቲካ ድርጅት ብቻ ሳይሆን ከቅርብ የአገራችን ታሪክም እጅግ እንዳራራቃቸው ገሀድ ነው። እርሳቸው ግራው ትውልድ ገደለው ብለው የሚከሱብትና በናፍቆት የሚያስታውሱን ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ህግ አክባሪነትን ብዕራቸው መልሶ መግደሉን የማስተዋል አቅም እንደተሳናቸው እንደኔ ላለው ተራ ዜጋ እንኳ ግልፅ ነው።

ዶ/ሩ የበቀሉበትን ህብረተሰብ የቅርብ ታሪክ በቁንፅሉ ጀምረው የአርባ ዓመቱን ማህበራዊ ቀውስ ያመጣብን አብዮት **"የፖለቲካ ባህላችንን ከምንጊዜውም በበለጠ ሰው በላ አድርጎታል" ይሉና፣ ቀጥለውም "ትላንት አንድ የኢሕአፓ ደጋፊ ሲገደል አናርኪስት ሞተ እንኳን ሞተ፣ አንድ የደርግ ደጋፊ ሲሞት ባንዳ ሞተ እንኳን ሞተ የታባቱ እንኳን ሞተ፣ አንድ የቀድሞ የአፄ ሃይለስላሴ መንግሥት ባለስልጣን ሲገደል እንኳን ሞተ ይህ አድህሪ እያልን እንድንል ያደረገን የግራ ርዕዮተዓለም እብደት …"** (ገፅ 2 ) ወዘተ አንተስዋል። እዚህ ላይ ዶ/ሩ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን ሆን ብለው ያድበሰበሱ ወይም ደግሞ ትውልዱን ለመዝለፍ በሚችሉበት ባዶ ስሜታዊ መንገድ መንጎዱን የመረጡ ይመስላል። አንደኛ በመንግስታዊ አዋጅና እቅድ    የተካሄደውን የደርግን የግድያ ዘመቻ ከአልሞት ባይ ተጋዳዩ የኢሕአፓ የመከላከል አርምጃ ጋር ሆን ብለው በአንድ የሞራል ፍርድ ይጨፈልቁታል። በመሆኑም አንድ ሰው ራሱን ለመከላከል ሲል ብቻ ሊገለው የመጣውን ቢገል ሁለቱም ወንጀለኞች ናቸው እያሉን ነው። በመሆኑም ደርግ በአካል የፈፀመውን ወንጀል እሳቸው በሞራል ደረጃ ይደግሙታል። ዶ/ሩ ከማህበራዊ ፍትህ ጋር የተጣሉ በመሆናቸው ይህ እውነታ ሊታያቸው አልቻለም።

ሌላውና በሁለተኛ ደረጃ ጨፍልቀው ያለፉት ፖለቲካዊና ታሪካዊ እውነታ አለ። ይኸውም በየትኛውም አገር ሆነ በማንኛውም ክንፍ የተመራ አብዮት የታለመበትን ግብ መታም አልመታም የዜጎችን የህይወት መስዋዕትነት ያልጠየቀበት ታሪካዊ ማጠየቂያ ማቅረብ አይቻላቸውም። በዶ/ሩ አቀራረብ ይህ አብዮት የሚባል ነገር እሳቸው እንደ መቅሰፍት የሚያዩት ጉዳይ እንዲያው ጥቂት የሚሰሩትን ያጡ ወጣቶች የሚያመጣውን እንይ በሚል መንፈስ ተነሳስተው ያመጡት አሪዌሊያን ቅስፈት አይደለም። የዶ/ሩን አላውቅም እንጅ የለውጥ ትልቁ ደመኛ ለሀገርና ለወገን መብትና ክብር በቅንነት ተነስተው በተመክሮ እጦት ስህተት የሰሩት ሳይሆኑ (ለዛውም ውድ ህይወታቸውን ሰጥተው) ወገኑ በአረመኔ ገዥ መብቱ ሲረገጥ አይቶ እንዳላየ ወይም ከሁሉም የለሁበትም ብሎ ተደብቆ ቆይቶ ብቅ ይልና ለሀገሬ ራዕይ አለኝ የሚለውን ሁሉ በጅምላ የሚያብጠለጥለው የህብረተሰብ ክፍል ነው።

በተፈጥሮው ለውጥን በማይሻው የዘውድ አገዛዝ አገራቸው ወደኋላ መቅረቷንና ህዝባቸውም የሚኖርበት አስከፊ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ሁኔታ ያንገበገባቸው እነ መንግስቱ ንዋይ፣ገርማሜ ንዋይ፣ ወርቅነህ ገበየሁ የመሰሉ ከተቀማጠለ ህይወታቸው ወርደው አገርን ለመታደግ ባደረጉት ሙከራ በስቅላት ተሰውተዋል። ያ ወቅት፡ ቀደም ሲል በነ ደጃዝማች ታከለ ወ/ሃዋርያትና በላይ ዘለቀ የመሰሉ አርበኞች፣ ቀጥሎም ከመኮንኖቹ ተደምሮ አንድ ትልቅ መዘዝ ወይም የታሪክ ጠባሳ ትቶብን አለፈ። ያም ለወገን ብለው እንደ ተራ ሌባ ተሰቅለው ሲሞቱ ወገን ቁጣውን ባለማሳየቱ የጀግኖች ሞት ከንቱ እየሆነ መምጣት ጀመረ። በመጨረሻም ይኸው ይህን ዶ/ር መሳዮችም ፈጠርን። ለማህበራዊ ፍትህ መቆምን ህዝባችን በባዶ እግሩ እየማሰነ ፊደል ያስቆጠረው ክፍል ውለታውን እንደመመለስ ነፃነቱን ለገፈፉትና ላስገፈፉት ሰባኪ መሆንን መርጠ። አመፅ አይበጅም፣ አብዮት የጥፋት ጎዳና ነው፣ ግራው አገራችን አጠፋ የሚሉና የመሳሰሉት የተለመዱ ወኔ ገዳይ ቋንቋዎች ይኸው ዛሬ ከአሳፋሪነት ወደ ብልህነት እየተለወጡ ነው።

ቅድመ የካቲት አብዮት ኢትዮጵያ ከመቶ 90 እጅ የሚሆነው ህዝቧ ከጅ ወደ አፍ የሚኖርና የተሟላ ምግብ የማያገኝበት አርሶ አደርን የያዘች፣ ከዚሁ እጅ በተለየና አስከፊ በሆነ ደረጃ ደግሞ የደቡባዊ ኢትዮጵያ ገበሬ በጭሰኝነት ቀንበር ስር የሚሰቃይባት፣ ሠራተኛው በውጭ ኩባንያ ባለቤቶች እጅ ለአስከፊ ብዝበዛና እንግልት የተጋለጠበት፣ ከመቶ 30 እጅ የሚደርሱ ህፃናት ዕድሜያቸው አምስት ዓመት ሳይደርስ የሚቀሰፉበት፣ በዛን ዘመን አገሪቱ በነበራት አነስተኛ የተማሪ ቁጥር አንኳ ሁለተኛ ደረጃና ኮሌጅ ያጠናቀቁ ስራ አጥ የበዛባት፣ ሴክተር ሪቪው በመባል የሚታወቀውን ትውልድ ገዳይ የትምህርት ስርዓት ለመተግበር ያነጣጠሩበት፣ ወታደሩ እኛ አገር ስንጠብቅ ልጆቻችን ተራቡ ብሎ

የደሞዝ ጭማር የጠየቀበት፣ የመሬት ስሪት ሕግ ይሻሻል የሚለው ሰላማዊ ጥያቄ በዘውዱ አገዛዝ የታፈነበት እና የመሳሰሉት እውነታዎች በአንድ በኩል፣

በሙስና የነቀዙ ባለባትና መኳንንት ታጅበው ስዩመ እግዚያብሄር ነኝ ይሉ የነበሩት ንጉሡ ነገስትም ለአገር እና ለወገን ደህንነት ደንታ አጥተው እጅግ ራስ ወዳድ በመሆን የቆየውን የንገሣዊያን ደንብ እንኳ ጠብቀው ለበትረ መነግስቱ ተረካቢ አጬ ለማውጣት እምነቱ ያጡበት። እንዲያውም ጃጅተው ሊመሩ የማይቸሉበት እድሜ ላይ በመድረሳቸው የስልጣናቸው ምሰሶ በላያቸው ላይ እስኪፈርስ የጠበቁት። የህዝባቸውን ረሃብና እንግልት (የወሎውን እልቂት ልብ ይሏል) የዳቦ ያለህ! የፍትህ ያለህ! ጬኸት ልባቸውን የማይነካው የንገሡ አስተዳደር በሌላ በኩል የቆመበት ሁኔታ ነበር።

በመጨረሻም እነዚህ ማህበራዊ ቅራኔዎች ሲብላሉ ቀይተው የንጉሱ ስርዓት በእንዳልካቸው መኮንን በተሞከረው የጥገና ለውጥ እንኳ ራሱን ማዳን አልቻለም። የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ከጥቂት ምሁራንና ተማሪዎች አልፎ የህብረተሰብ ጥያቄ እየሆነ የመጣበትና የመንግሥት ጥያቄ በጥገና ለውጥ የማይመለስ ጉዳይ ሆነ። ከላይ የተጠቀሱትን ውጥረቶች አርግዛ ስታምጥ የቆየችው ኢትዮጵያ የየካቲት 66ን ግብታዊ አብዮት ወለደች። ዶ/ሩ እጅግ የሚጠሉት አብዮት የተወለደውም ያኔ ነው። እነዚህ ሃሳዊ ምሁራን ያለፈውን የዘውድ አገዛዝ ለውጡን ካጨናገፈው ወታደራዊ አስተዳደር፣ ወታደራዊውን አስተዳደር ከወያኔ ጋር በማወዳደር የፊተኛው ከኋለኛው ይሻለን ነበር፣ ግራው ክፍል ነው ይህን መቅሰፍት ያመጣብን በሚል ታሪክን እየከለሱ የሚገኙት። ምን እያሉን ነው? ተራማጁ ምሁርም ሆነ ማህበራዊ ፍትህ ጠያቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሶስቱን አገዛዞች በመደዳ አሰልፎ ይህኛው ይሻለናል ብሎ ያመጣው እያሉን ነው?

የሚያሳዝነው ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር ተጨባጭ የሆነውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በራሳቸው ታሪካዊ ወቅትና ሁኔታ ከማቅረብ ይልቅ በእንዶድ አጥበው ግልብ ስሜትን ለማስተናገድና ያን ትውልድ የታሪክ ተወቃሺ ከማድረግ ስሌት ተነሳስተው ሁሉን ነገር በጭንቅላቱ ሲያቆሙት ይታያል። አንድ አንድ ባህላዊና ማህበራዊ ሀረጎችን መርጠው ይመዙና የዛሬን አያርገውና አገራችን እንዲህ ነበር እኮ ብለው ኡኡታ ያስደምጣሉ።

ዶ/ሩ እንዲህ ነበር ይላሉ **“አብዮት በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ በጎ ባህላዊ  እሴቶችን አጥፍቷል (በህግ አምላክ የመሳሰሉትን ዘመን ተሻጋሪ የነበሩ ጥልቅ የህግ አፍቃሪነታችን መግለጫወች ጠፍተው በእነሱ ምትክ አብዮት ከምንም ነገር በላይ ናት፣ አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚሉ ብሂሎች ተነሱ)። በዚህ አይነት የሰውን ልጆች ነፃ አወጣለሁ ያለው አብዮት የነፃነት መሠረትና መግለጫ የሆነውን ሰብዓዊነት ከማህበረሰባችን ባህል ወስጥ ጭራሹኑ አጠፋው”** ይህን መሰል እጅግ የተለጠጡ ክሶች የማህበራዊ ለውጥ ሂደትን በመርህ ደረጃ ተፃራሪ በመሆን የቀረበ ከንቱ መከራከሪያነት ውጭ አብዮቱ በጎ ባህልን ለመምታት የታለመና ያነጣጠረ አልነበረም። ያንንም አላደረገም።

የዶ/ሩ መርጦ የማስታወስ አቀራረብ እንዳለ ሆኖ የወገናችን የራስ ገዝነት ችሎታ ከአብዮት በፊት ወይም በኋላ በሚል የሚገደብ አይደለም። በ1983 ዓ.ም (አብዮቱ ከተካሄደ 17 ዓመት በኻላ) በደርግ መበታተንና በወያኔ አገሪቱን ፀጥታ መቆጣጠር ባልቻለበት 6 ወር አስከ ዓመት በነበረው ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ መንግሥት በሌለበት ራሱን በራሱ የማስተዳደር (ህግን አክባሪነት) ባህሉ ከወገን አልፎ ዓለምንም ያስገረመ ነበር። ቀጥሎም በ1997ቱ ምርጫ በሚሊዮኖች የሚቆጠረው አርሶ አደር ብዙ ኪሎ ሜትር ተጉዞ 14 ሰዓት በትዕግስት ተራ ይዞ ድምፁን የሰጠበት፣ ድምፀንም የሰጠው ወያኔ ባሰመረለት ዘረኛ የጎሳ ስሌት ሳይሆን በብሄራዊ ጥያቆዎች ዙሪያ ነበር።  ዶ/ሩ ለአገሪቷ ከሞቱላት በላይ ተቆርቃሪ ነኝ ብለው ያዙን ልቀቁኝ ስለሚሉ ሰከን ያለ አዕምሮ የማይስታቸውን አውነታዎች ቢስቱ አይገርምም። ለግራው የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸው ጥላቻ እንዳለ ሁኖ ግን ከዛ ያለፈ መልካም አማራጭ ነው የሚሉትን የራሳቸውን አመለካከት ለመጠቆም ድፍረቱን አላገኙም እንዲያው ብቻ “ግራው” እና “አብዮት” የሚባለውን አታንሱብኝ ውቃቢየ አልወደደውም አይነት ነው።

ዶ/ሩ በገፅ 3 ስለ ኢሕአፓን እንዲህ ይላሉ **“በ1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን አብዮታዊ ሁኔታ በመምራት የኢትዮጵያን ህዝብ ነባር ችግሮች እንፈታለን በማለት በርካታ የግራ አመለካካት ያላቸው ድርጅቶች በአብዩቱ ወቅት ብቅ ብለው ነበር። ከነዚህ በወቅቱ ብቅ ብለው ከጠፉትና በወቅቱ በተለይ በከተሞች አካባቢ ያሉትን በርካታ ትምህርት-ቀመስ ወጣቶች (የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች) ትኩረት ከሳቡት ድርጅቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) የሚባለው ድርጅት ነበር።”**  ስለዚህ ኢሕአፓ አንድ ሰሞን ብቅ ብለው ከጠፉት የግራ አመለካከት ከነበራቸው ድርጅቶች አንዱ ነበር እያሉን ነው። ስለሆነም ኢሕአፓ የለም ጠፍቷል ማለታቸው ነው።

**ዶ/ሩ** ለዚህ ድርጅት ያላቸው ከፍተኛ ጥላቻ ከሰይጣንም ያስተቃቅፋቸዋልና ለዚሁ እምነታቸው የሚጠቅማቸው መስሎ ስለታያቸው በኢህአፓ ውስጥ ቡድን ፈጥረው የተንቀሳቀሱና ፓርቲው ዓልሞ የተነሳበትን የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ (የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ) አጥፈው ከደርግ ጋር እንቀላቀል ደርግም እናንተ እንደምትሉት ፋሽስት አይደለም ብለው፣ በሚስጥር (ፓርቲው ዓመራር ሳያውቅ) ከወታደራዊ መንግስት ባለሚሎች

በነ ብርሃኑ ዘሪሁን፣ የጌታቸው ማሩ ወንድምና የተፈሪ ባንቲ ረዳት መኮንን በነረው መለሰ ማሩ በኩል ደርግን ለመቀላቀል እየጣረ የነበረውን ብርሃነ መስቀል ረዳንና ጌታቸው ማሩን (የወጣቱን ድርጅት መሪዎች በሚስጥር ሰብስቦ በፓርቲው ላይ ያሳመፀው) ታላቅ ስራ እንደሰሩ አጉልተው ለማሳያት ሞክረዋል። ብርሃነ መስቀል ከአንጋፋ የተማሪው እንቅስቃሴ መሪዎችና የፓርቲው መስራች ዓባል የነበረ ሲሆን ፣ ጌታቸው ማሩ አብዮት የሚባለውን ግሩፕ ወክሎ ከፓርቲው የተወሃደ ነበር። ሁለቱም ምለው የተነሱበትን ዓላማ እና የፓርቲ ህግ ጥሰው አንጃ ፈጥረው (አንጃ የሚለው ስድብ አይደለም ዶ/ር እርስዎ በሚፈቅዱት የፖለቲካ ባህል Faction የሚለውን ቃል ተክቶ ነው) ከጠላት እስከወገኑበት ጊዜ ድረስ የነበራቸውን አዎንታዊ አስተዋጽዖ ማንም የሚሺርባቸው አይኖርም።

ክህደትና የሃሳብ ልዩነት ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ልዩነቶች ደግሞ የሚቻቻሉና የማይቻቻሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የፓርቲውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስና ብሎም ይህ ካልሆነ ብሎ በድርጅት ላይ ቡድን የሚያስባስብ ልዩነት፣ ከትግሉ መርዘምና አሰልችነት በመዳከም ፓርቲውን ሊያጠፉ ከተነሱ ሃይሎች ጋር በመለጠፍ በፓርቲው ባለሚሎች ላይ የሃሰት ክስ ይዘው የተነሱ ልዩነቶ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአሠራርና ታክቲክ ላይ የሚነሱ መለስተኛ ልዩነቶች ይኖራሉ። ሁሉም አይነት ልዩነቶች የሚስተናገዱት በፓርቲው ዴሜክራሲያዊ መድረኮች ሲሆን የሚዳኙት በድርጅቱ ዓባለት ጠቅላይ ጉባኤና የፓርቲው ህገ ደንብ መሠረት ነው። እንዲያው በደፈናው የልዩነቶቹን ምንጭና ሂደት ሳያውቁ ልዩነቶችን መቻቻል በሚል ሀረግ ጠርዞ ዳር ቆሞ ማራገብ ከተራ ልወደድ ባይነት (populist) ሌላ ትርጉም የለውም።

እርስዎ ገና የወጣቱ ድርጅት ዓባል ሆነው ከከፍተኛ እስር ቤት ብዙ ሳይንገላቱ የኮለኔል ዳንኤል ባለቤት በነበሩት እህትዎት አማካኝነት ወደ ኪውባ እግሬ አውጪኝ ብለው መውጣትዎንና የፓርቲ ዓባል እንዳልበሩ እንድማናውቅ ባይቆጥሩን ጥሩ ነው። ስለዚህ የኢህአፓ ዓባል ነበርኩ እያሉ ከአንድ ሰሞን አፍሮ ፋሺን ባልተለየ ነካክቶ ያለፈው ብቻ ሳይሆን፣ ጭራሽ ሲያልፍም ያልነካቸው ፀረ-ኢህአፓ ካድሬዎች ሁሉ ነበርኩ ብለው ቢቀርቡ ማጥቃቱ ተቀባይነት የሚያስገኝላቸው መስሎ ስለሚታያቸው የተለመደ አቀራረባቸው ሆኗል። እንደ ኢሕአፓ ያሉ በሰላማዊና መንገድ የመታገል መብታቸውን የተነፈጉና ብሄራዊ ጠላት ቁጥር አንድ ተብለው ተፈርጀው በከፍተኛ ጥንቃቄ በህቡ መስራት የተገደዱ ድርጅቶች ሚስጥራዊ አሰራር ተራ አሉባልታን ለሚያናፍሱባቸው አመችነት አንዱ ችገራቸው ነበረ። አሁንም ነው።

ለመሆኑ ደ/ሩ ካሁን ቀደም በፃፉት መፅሀፍ ቢጤ፡ **እነ ብርሀነመስቀል፣ ዘሩ ክሸንና ሌሎች የትግራይ ልጆች የተማሪውን እንቅስቃሴ ለሻዕቢያ መሳሪያ አደረጉት። ትግሬዎች ሁሉ የሻዕቢያ አሽከሮች ናቸው ።**ብለው በከሰሱበት አንደበት ዛሬ ደግሞ በትግል ላይ ያለውን ድርጅት ኢሕአፓን ለመምታት ሲሆን ለደርግ ያደረውን ብርሀነመስቀል ትክክለኛ መንገድ የያዘ እንደነበር የሀሰት ምስክር ለመሆን መረጡ። ዶ/ሩ የፖለቲካ ጋብቻቸው ሁሉ ቶሎ በመፋታት የታወከ ነው። መጀመሪያ ከእራሱ ከኢህአፓ፣ ወያኔ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ቡድን ወደሌላ እንደ ፌንጣ ሲዘሉ የቆዩ ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ ከሞረሽ ጋር ሆነዋል። ግለሰቡ እንዲያው ተፈጥሮ ባላደላቸው ጉዳይ ውስጥ ገብተው ባተረፉት የስነ-ልቡና ኪሳራ ምክንያት በአቋማቸው ፀንተው ያዩአቸውን አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዓመራር ዓባል- ግለሰብ ጓንታቸውን አውልቀው በማብጠልጠል የፖቲካው መሀመድ አሊ ነኝ ሊሉ ይቃጣቸዋል።

ዶ/ሩ እኛ አገር እንዳለው የሰው በላ ስርዓት ባለበት ሁኔታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ የህቡዕ እንቅስቀሴ ቀርቶ በውስጡ ስላለው አሠራር የመጀመሪያ እውቀት ያላቸው ሳይሆኑ፣ በሁሉን አውቃነት ግራውን ቀኙንም በደፈናው የሚከሱ ናቸው። ሁሌ ተቃዋሚውንም አገዛዘዙንም በአንድነት ሲያተራምሱ ከመኖር ሌላ እስቲ እሳቸው ከነ አቶ እያሱ አለማየሁ ምን የተሻለ አርዓያነት አሳይተው ነው? ለየትኛው የፖለቲካ ፓርቲ ቅን አገልግሎት ሰጥተው ነው ወይም መርተው ነው?

እሳቸው እንደሚያወድሱት የመቻቻል ፖለቲካ (the politics of accommodation) ከሚሰብኩት ምዕራባዊያን (አሜሪካንንም ጨምሮ) ጋር ይምታታባቸዋል። የኻለኛው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አነሰም በዛም ከውጪ ፖሊሲና ብሄራዊ ደህንነት ከሚሉት ጉዳይ በመለስ ያሉትን ልዩነቶች ለማስተናገድ የበለፀጉ ተቋማትና የህግ የበላይነት ያለበት ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግን ተቃዋሚ የመሰለውን ለማጥፋት በአንድ ሌሊት በአንድ ሰው ህግ የሚያወጣበት አገር ነው።

በጌታቸው ማሩ አሟሟትም ዙሪያ የሚያናፈሱት ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ መሠረታዊ አመክኖን የሚጠቀም ሰው መጠየቅ ያለበት ይህንን ነው፡ ፓርቲው ጌታቸው ማሩ እንዲገደል ከፈለገ እንኳን እስረኛ ይዞ እራስንም ለማዳን በማይቻልበት ቀውጢ ጊዜ ለምንድን ነው እሱን ከአንድ መጠለያ ቤት ወደ ሌላ እያዘዋዎሩ ያስቀመጡት ብሎም ቤቱ በደርግ ፀጥታዎች እስኪበብና በዚሁ ግርግር ለማምለጥ እስኪሞክር የሚያቆዩት? የራሳቸው የክህደት ታሪክ እያባነናቸው የኢሕአፓንም ታሪክ ያጠቆሩ እየመሰላቸው ቆራርጠው ገደሉት፣ አሲድ ረጩበት፣ ወዘተ የሚል ስዕል ሊስሉ ሞክረዋል። ይታያችሁ በዛን ዘመን በሰው በላው የደርግ የፀጥታ ሃይል የኢሕአፓ ዓባላት ሲከበቡ በማንኛውም መንገድ ማምለጫቸውን ከማሰብ ይልቅ ጌታቸው ማሩን ገለው፣ ሰውነቱን የመቆራረጥና በአሲድ ለማቃጠል ጊዜያቸውን ሲወስዱ?

ዶ/ሩ መርጠው ማስታዎስ የሚወዱ በመሆኑ እንጅ በፓርቲው ሰራዊት ውስጥ እንኳ አንድ የሰረዊት ዓባል ከሠራዊቱ መውጣት ሲፈልግ ከመሸኛ ገንዘብ ጭምር ሰጥቶ ያሰናብት የነበረ የታጠቀ ሃይል በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ድርጅት ኢሕአፓ/ኢሕአሰ ነው። ኢህአፓን ሁለት የተለያዩ መርሆዎች ይገዙት ነበረ ሊሉን ይሆን?

የፊውዳሉን የበሰበሰ ስርዓት ናፋቂ፤ የወታደሩ አገዛዝ ጥፍር ነቃይ፣ የቅኝ ግዥዎ ቅጥረኛ (ተገንጣዩን አወናባጅ ምሁር ነን ባዩን ጨምሮ)፣ የጥቁሩ ህዝብ ማፈሪያ ወያኔዎች ወዘተ በጠቅላላ ፀረ-ኢሕአፓው ክፍል ድርጅቱን አጠፋለሁ ብሎ ራሱን ያጃጅል እንጅ፣ ኢሕአፓ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ብሄራዊ ተቋም በመሆኑ በሚጠሉትና በሚፈሩት ከንቱ ህልም የሚወገድ ድርጀት አይደለም ።አንድ ቀን ይህ ክፍልና ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ቆመው ማንኛውን ተጠያቂ እንደሚያደርግ የምናይበት ቀን ይመጣል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። እነዚህም ክፍሎች ይህ ቀን ከመድረሱ በፊት ከበደሉት ህዝብ ይቅርታ ቢጠይቁ ይሻላቸዋል። በኢትዮጵያ ሉአላዊነት አልደራደርም ያለውን ክፍል ማጥቃት ስራየ ብለው ለተያያዙትም ልቦና ይስጣቸው ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

መዝገቡ ገበየሁ